# ድንቁርና

By: Cosmos-2000, April 2009

ከወደላይ አግበስብሶ ከወደታች አስወልቆ
ጨምደድ አርጎ እንዳታመልጥ ተጠንቅቆ
በስልጣኑ ተዘባኗል በሙስና ተዘፍቆ::
በሆድ እንዲገዙ እንዲሰገዱለት ልቡ ጓጉቶ
መጪው ትውልድ ባዙሪቱ እንዲጠመድ ልቡን ስቶ
በጠመንጃ እንዲሸበር ነብሰ-ገዳይ አሠማርቶ
ተቆርቋሪን አባረረ ከግፍ ላይ ግፍ ቤቱን ሠርቶ::
መክሮ ዘክሮ ሃሰት ፈጥሮ ሞኛ ሞኙን አስጨብጦ
ዕውነት ይቻት ሲል ከረመ እንዳታመልጥ ተደናግጦ::

ስስት ተንኮል ከስልጣን ጋር ተጣላልፈው ነገሱበት
ሕግ አውጥቶ ተበተበው ሥልጣን ወዶ ዘመተበት::
አዛዡ እርሱ ተርጓሚ እርሱ ፈራጅ እርሱ መራጭ እርሱ
ገዳይ እርሱ ሌባው እርሱ ወሳኝ እርሱ ትርፉም ለርሱ
ጥቂት ተለጣፊዎች አጨብጭበው በሚያምሱ
ሕዝባዊ ስርዬት ጠፋች አልተቻለም መተንፈሱ
ዴሞክራሲ ብኾ ሆነች እያቦኳት እየለወሱ
አበላሿት መልኳ ጠፋ ከሕዝብ ጋራ ሲረሳሱ::

ሕልም አያውቁ ሕልም አይፈቱ እኒያ ያልታደሉ
ተልዕኳቸውን ለማሟላት ደንቆሮችን ያመርታሉ::
የኛን በኛ አስተካክለን ባመኔታ እንዳንወያይ
ጥፉ ተባልን በደደቦች ባስመሳዩ ባገር ገዳይ
ደንቆሮ ፈረደብን ላዩን አይቶ ውስጡን ሳያይ::

እኔን የሚያናደኝ ሚጃጃለው ያ ደንቆሮ

እኔን ያሳዝነኝ ሃሰትን የሚያጅበው በከበሮ
መብት የለችም እንዲህ አርጎ አደናግሮ
ፍትሕ አትኖር እየጣሳት ተንደርድሮ::

ጥበብ አልባ አፋለሱት ፈሩን ስተው እየዋለሉ
ይኸው ዛሬ ከሃዲ! ባንዶች! ይላቸዋል አገር ሙሉ::
እነርሱማ ግዙፍ ስህተት እንደሠሩ መች ያምናሉ?
ለሕዝባችን ባስረዳነው በላይ ሆነው ይቆጣሉ
የፊሲታ ተቆጢታ ስንላቸው በስጨት አሉ
ግፋ ቢል ችግር ፈጥረው አቃቅረው ይሄዳሉ
ግን ማስተካከል የኛ እንደሆን እናውቃለን በጥቅሉ::

ካያያዝ ይቀደዳል ካነጋገር ይፈረዳል አሸው ሲሉ
ለብቻቸው ዘር ለይተው ላይካካዱ ተማማሉ
በቅናት በጥላቻ በስግብግብነት የታጀሉ
በቃህ በሉት እንጅ ሃገር ዘርፈው ፍርድ ሲያጓድሉ::

ፍቅር ሃሳብ መሆኑን ሳያውቅ በየበረሃው ተሽፍቶ
በትግሉ ሰዓት እኛ ለኛ በኛው ብሎ ማሰብን አስቀርቶ
በደም ታጥቦ አቃቃረ ነጣጠለን ተቆጥቶ::
አቤት ጭካኔው ርኅራኄ በልቡ አይታይም ምልክቱ
አትሞኙ ከቶ አይድንም ተለውጧል ሰውነቱ
ያጠፋውን አስታውሱ የደራውን ዝርፊያ በያይነቱ
እያፋጨ የሚያጋጨው የተናጋው አንድነቱ
ጭፍን ታዛገሮ ቹ ፈጥነው ይደርሳሉ ለጥፋቱ
ዓይተነዋል አይዋዛም ሳትጥሉ እንዳትሞቱ::

እድገታቸው በኛው ሃገር ምቀኞቹ አሰሯቸው
የነጭ ሃገር ለማየትም እንደ እኔ ዕድል ሳይገጥማችው

ኖረው ቢሆን እስከ ዛሬ ይዘልቅ ነበር ጥበባቸው
ድሮስ ቢሆን አድናቆትን አስገኝቷል ጽሁፋቸው
ስለቀኑ በዕውቀታቸው ደብዛቸውን አጠፏቸው
ይፈቱ ማለት ነውር ሆኖ ምሁራኑም ረሷቸው
እኛ ለእኛ መቆርቆሩ ነውር መስሎ እየታያቸው ::

ፍቅር ሲያረጅ ጓሮ ጓሮውን ይሄዳል እንዲለያይ
አገር ሲያረጅ ሆዳሞቹ ይፈላሉ እንደ ተባይ
አሮጌው ጠፍቶ አዲስ ይምጣ ተሻሽሎ ተመልምሎ
ሳትበጣጥሱ አያይዙት ጤና አይሰጥም ተነጣጥሎ
ደንቆሮ ማየት አይችል ሰብሰብ አርጎ አጠቃሎ::

የኛን ዕድል እየነጠቁ ለራሳቸው ዕድል ሲወስኑ
ሃሳብ አንሰጥ መብት የለንም ዓይናችንን እየጨፈኑ
መብት ከሌለ አገር የለም ታዲያ ቁልጭ ነው እያዘኑ::
እስቲ ተመልከቱ ተለጣጥፌው ሲባደኑ
የኛን ሰጥቶ ከኛ ወስዶ ባዶ አስቀረን ምና ምኑ::

ደንቆሮችን በየተራ ተከታትለን ለዘመናት
ጉሮሮ ለጉሮሮ እየተናነቅን ለ40 ዓመታት::
ለግፈኛው አሜን ብሎ አደግድጎ ጉብ አለበት
ሆድ አደሩ አስመሳዩ ባገሬ ላይ ፈነጨበት
ተቀጥላ መሆን መርጧል የጀሮ የዓይንና የአንደበት::

ማየት ከፉ በፍትሕ ላይ መቃብእር ሲሠሩባት
ጀግና ሞልቶ ታሪክ ሠሪ ግን አድርባዮች ነገሡባት::
ዛሬስ ጠፋ መሰል የሚፋለም ለፍትሕና ለነፃነት
በግንባር የሚዋደቅ እንድንላበስ ሰብዓዊነት
ነፃነትም ድምጿ ራቀ ትሙት ትዳን ማን ጠይቋት?

አትነሳም ጀግና እስኪገኝ ለአንድነቱ የሚሟት
መተኛትስ ወግ ነበረ እንዴት ትንቃ ማን ቀስቅሷት
አፈፍ ብላ እንዳትመጣ ጮክ ብለው መቸ ጠሯት::

ዓይኖቻቸው ብር ያዩቱ ቀልብ አጥተው ቀባጠሩ
ነጻ ሳንሆን አትምጡብን የሌለንን አትቁጠሩ
ዓይን ለዓይን እየሸጡን ይመጣሉ ሊያደናግሩ
ሃቅን ለመደበቅ ሌትም ቀንም ሲሞክሩ
ታዘብናቸው ደንቆሮችን ተምረውም ያልተማሩ::

የነርሱው የኛ አይደለም ተናግሯል የወርቅ ዘሩ
የኛ የምንለው እንደሌለን እናያላን ካሠራሩ
ታሪካችን አይገናኝ ብሎን የለ ከጅምሩ
ከመቶ በላይ ስንቆጥር ይጀምራል ክርክሩ::
ወርቂማ ወርቅ አግኝቶ ደኅና አድርጎ መዘበረ
ወርቅ ካልሆኑ ወርቅ አይሰጥ ይኸው ቁርጡ ተነገረ
በወርቅ ዘር በወርቅ ጥሪት ወገናችን ተደፈረ
የብረት ሃይል አኅበጠው ከትከሻው ተሠበረ::

ተወናብደው ወደ እነርሱ ሚለጠፉት ሞኞች ናቸው
ድንቁርና ተጭኗቸው ርኩስ መንፈስ ተጣብቷቸው
ስናጋልጥ ሐቅ ይዘን ነው እንዳይቀጥል በጥፋቱ
አንሸጥም አገራችንን እኛ እኮ ነን ባለቤቱ::

አየ አንድነት መሬት ሸጡ እንዳሻቸው
ታዛገቡማ የኛው ጅል ነው በመፈረም የሰጣቸው::
አየ ዳኝነት! ስንቶቹ ሸባ ሆኑ ግርፋቱ ጸንቶባቸው
አየ ዴሞክራሲ! እያካበቡ እንደከብቶች ሲያጉሯቸው
አየ ፍቅር ዘር ሲያጠፉ እንደሰው ልጅ አይቀፋቸው::

ባባት አደሩ በተለምዶ ብንሰጣቸው ሙሉ ክብረት
ተላላኪው ቡታ ሰዶ አቃብሩን ሲል ገና ሳንሞት
ጥቂት ምሑራንም አሽቃበጡ ጀሮ ሰጡት
አፈር ሊያለብሱን ተሯሯጡ ከመቅጽበት::
ለካስ የምሁር ደንቆሮ አለው መኖር ሚመርጥ አጎብድዶ
አትጠራጠሩ እንደሚኖር ብዙ ትምህርት ግን ዕውቀት ባዶ::

ቃል ያድናል! ቃል ያጠፋል! ሲመረጥም ተጠንቅቆ
ቃል ከቃል ጋር ተፋጭቶ ተብላልቶና ተደባልቆ
ለመበቀል አሰላስሎ ጣልቃ ገብቶ አጨናንቆ
የዚህ የዚያም ምኞታቸው ተጨምሮ ተጨፍልቆ
ተንፈስ እስኪል ይጎፈላል ቱግ እያለ ተፈንጥቆ::

ሞት አይቀርም ግን አሟሟቴን አሳምረው
ጥንትም ሆነ ዛሬ ሲባል ኖሯል ባገሬ ሰው::
የነርሱ ሞት ይዞ ሚሞት አዲስ ተስፋ የማይተካ
እኛ ብንሞት እንዲያያዝ ነፃ ሆኖ እንዲረካ
አሟሟትን የማያውቁ ባገራችን አሉ ለካ
ምን እንዳይቀር ይጋለጡ ስታዩአቸው ንፉ ፊሽካ::